Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# ስለ AstraZeneca ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት

ወቅታዊ የሆነበት ቀን: 30 ሐምሌ/July 2021 ዓ.ም

## ስለ ክትባቱ

የAstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ሰዎችን ከኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ መከላከል ይችላል። በዚህ ክትባት ማንኛውንም ህይወት ያለው SARS-CoV-2 ቫይረስን አያካትትም እንዲሁም ለርስዎ ኮቪድ/COVID-19 አጋልጦ መስጠት አይችልም። ስፓይክ ፕሮቲን/spike protein ለተባለ የSARS-CoV-2 ቫይረስ ጠቃሚ የሆነ አካል የጀነቲክ ኮድ ዝርያን ያካተተ ነው። የስፓይክ ፕሮቲን በመደበኛ ጉንፋን "ተሸካሚ" ቫይረስ (የአደኖቫይረስ/adenovirus) ላይ እንደገባ ነው። የአደኖቫይረስ ተሸካሚ በሰውነትዎ ሴሎች/ህዋስ ላይ ስፓይክ ፕሮቲን ስለሚያመጣ፤ መጀመሪያ ስለ ስፓይክ ፕሮቲን ማንበብ መቻል እንዳለባቸውና ቅጂውን ማግኘት ይኖርባቸዋል። ከዚያም የርስዎ በሽታ መቋቋም ህይል አሰራር ቫይረሱን በመገንዘብ ከSARS-CoV-2 ቫይረስ ጋር ይዋጋል። የአደኖቫይረስ ተሻሽሎ ስለተለወጠ አንዴ በሴሎች/ህዋስ ውስጥ ከሆነ ሊባዛ አይችልም። ይህ ማለት ወደ ሌሎች ህዋስ እንደማይሰራጭና ብክለትን መፍጠር እንደማይችል ነው።

ክትባት መውሰድ በፈቃደኝነትና ያለክፍያ በነጻ ነው። ስለ ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ለማንኛውም አሳሳቢ ጉዳይ ወይም ጥያቄዎች ካለዎት ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት ከርስዎ የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ እና/ወይም ከርስዎ አጠቃላይ ሀኪም/GP ጋር መነጋገር ይችላሉ።

ለ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት መጠቀም የሚቻለው እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ድህንነቱ የተጠበቀና በጥሩ እንደሚሰራ ነው። የAstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ በጣም አነስተኛ ችግር 'ትሮምቦሲስ ከትሮምቦሳይቶፐኒያ ጋር/thrombosis with thrombocytopenia syndrome' (TTS) የተባለ እንደተፈጠረ ሪፖርት ተደርጓል፤ ይህም የደም መርጋትን እና የአነስተኛ የደም ፕላተለት/platelet መጠን ደረጃ መቀነስ ይሆናል። ክትባት በመውሰድ የሚገኘው ጥቅም በዚህ ሁኔታ ከሚፈጠር ችግር በጣም የበለጠ ነው። በወጣት ጎልማሶች ላይ TTS በጣም የተለመደ ነው፤ ስለዚህ ይህንን ችግር ለመቀነስ Comirnaty (Pfizer) ክትባትን መውሰዱ ይመረጣል፤ እድሚያቸው ከ60 ዓመት በታች ለሆኑ ጐልማሶች እና በሰረብራል ቨኑስ ሲኑስ ትሮምቦሲስ/ cerebral venous sinus thrombosis (የአንጎል መዘጋት ዓይነት) ታሪክ ላለባቸው፤ የሀፓሪን ማነቃቂያ ትሮምቦችይቶፐና/ heparin induced thrombocytopenia (ለሀፓሪን ህክምና አነስተኛ ችግር)፤ ኢዲኦፓቲክ ስፐላንክኒክ ትሮምቦሲስ/idiopathic splanchnic thrombosis (በሆድ እቃ ቨን ውስጥ ደም መርጋት) ወይም አንቲፍፐስፎሊፒድ ስይንድሮም/antiphospholipid syndrome ከትሮምቦሲስ ጋር ላለባቸው ሰዎች የComirnaty (Pfizer) ኮቪድ/COVID-19 ክትባትን መውሰዱ ይመረጣል።

## ክትባት በመውሰድ ጥቅሞች

የ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰድ ከኮቪድ/ COVID-19 ህማም ይከላከላል። በተለይ ከከባድ ህመም፤ ሆስፒታል ከመግባትና ከሞት ይከላከላል። በሁለቱም በክሊኒካል ሙከራዎች (ለጥቅም ከመመዝገቡ በፊት) ክትባቱ በከፍተኛ እንደሰራ እና በእንግሊዝና በስኮትላንድ ውስጥ 'በትክክለኛ ዓለም' ላይ ክትባቱን በወሰዱ ሰዎች ላይ እንደተጠናው በጥሩ እንደሰራ ነበር።

ኮቪድ/ COVID-19 በጣም ከባድ በሽታ እንደሆነ ይህም በሁሉም እድሜ ገደብ ላሉ ሰዎች ከባድ ህማም ሊፈጥር ይችላል። በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሞት ምክንያት እንደሆነ እና በመቶ ሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ በዓለም ውስጥ ለከፍተኛ ተላላፊ በሽታ ምክንያት እንደሆነ ነው። ክትባት መውሰዱ የሚረዳው ለኮቪድ/ COVID-19 መሰራጨት በመቀነስ ለሁለቱም ማለት ግለሰቦች እና በማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ ሰዎች በሙሉ ለመከላከል ይረዳል።

## ይህን ክትባት ማን ማግኘት እንደሚችል

እድሚያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑት ሰዎች ለ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ማግኘት ይችላሉ። እድሚያቸው ከ< 60 ዓመት በታች ለሆኑት ሰዎች ከAstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ባሻገር የ Comirnaty (Pfizer) ክትባትን ቢወስዱ ይመረጣል። ይሁን እንጂ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባትን መጠቀም የሚቻለው እድሚያቸው ከ< 60 ዓመት በታች ለሆኑ ጎልማሶች ሲሆን ይህም የComirnaty (Pfizer) ክትባት ከሌለ እና ግለሰቡ ስሊከሰት ስለሚችል ችግር እና ጥቅሞች ከተረዳና በራሱ ከወሰነ ነው። በወረርሽኙ ቅንጅት ጊዜ እድሚያቸው ከ< 60 ዓመት በታች የሆኑት ጎልማሶች ለComirnaty (Pfizer) ክትባት ማግኘት ካልተቻለ የAstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባትን ለመውሰድ በጥልቀት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

## ክትባት በመሰድ የሚፈጥሩት ችግሮች

እንደማንኛውም ክትባት የኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ አንዳንድ ጊዚያዊ የሆኑ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። የ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ የሚፈጠር ከተለመዱት የሚካተት: መርፌውን በተወጉበት ቦታ ህመም ወይም መጠዝጠዝ፤ የጅማት ህመም፤ እና ትኩሳትና መቀዝቀዝ ይሆናል። አብዛኛው የሚፈጠር ችግር መካከለኛና ጊዚያዊ እንደሆነ፤ በ1-2 ቀናት ውስጥ ይጠፋል።

### ትሮምቦሲስ/Thrombosis ከትርምቦስይቶፐኒያ/thrombocytopenia የበሽታ ምልክት (TTS)

የAstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት በትሮምቦሲስ ከትሮምቦስይቶፐኒያ በሽታ ምልክት/(TTS) ተብሎ ከሚጠራ የሚፈጠር በጣም አነስተኛ ችግር ጋር የተገናኘ ይመስላል።

#### TTS ምንድ ነው?

በ TTS ላይ የሚካተተው የደም መርጋት (thrombosis) እና አነስተኛ የደም ፕላተለት/platelets (thrombocytopenia) ሲሆኑ፤ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ በ 4 እስከ 42 ቀናት ባለው ጊዜ ይከሰታል። የደም መርጋት በተለያየ የሰውነት አካል ማለት እንደ አንጎል (ሰረብራል ቨኑስ ሳይነስ ትሮሞሲስ/cerebral venous sinus thrombosis ወይም CVST ተብሎ በሚጠራ) ወይም በሆድ እቃ ውስጥ (idiopathic splanchnic thrombosis) ሊከሰት ይችላል።

TTS መከሰት አነስተኛ እንደሆነ ነገር ግን በሰዎች ላይ በጣም እንዲታመሙ ሊያደርግ እንደሚችልና ለረጅም ጊዜ የአካል ጉዳተኛ ወይም ለሞት ያዳርጋል።

ለ TTS አሰራር ዘዴ ምክንያት የሆነው ሙሉ በሙሉ አልታወቀም፤ ነገር ግን ከሀፓሪን ማነቃቂያ ትሮምቦችይቶፐና/ heparin-induced thrombocytopenia (ወይም HIT) ጋር ተመሳሳይ ይመስላል፤ መጠነኛ ምላሽ መቋቋም ለሀፓሪን/ heparin ህክምና ይመስላል።

#### በ TTS ችግር ፈጠራ ላይ የበለጠ ማንኛውም ቡድኖች አሉ ወይ?

በአውስትራሊያና ውጭ አገሮች ውስጥ ለ TTS መጠን ደረጃ ሪፖርት እንደተደረገው አብዛኛው ችግር የተፈጠረው በወጣት ጎልማሶች እንዲሁም በሴቶች ላይ በበለጠ የተለመደ እንደሆነ ነው። ይሁን እንጂ ሪፖርት እንደተደረገው በወንዶችና በእድሜ ትልቅ በሆኑት ሰዎች ላይ ችግሩ እንደተገኘ ነው። ሴቶች በከፍተኛ ችግር ላይ ስለመሆናቸው እስካሁን ግልጽ አይደለም።

አሁን ባለው መረጃ፤ ለ TTS መፈጠር አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል ወይም ከተፈጠረ ሊያባብሰው የሚችል ቀደም ያለ የጤና ሁኔታ ስለመኖሩ ለይተን አናውቅም።

#### በአለፈው ጊዜ የደም መርጋት ችግር ለነበረባቸው ሰዎች የAstraZeneca ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀ ነው ወይ?

ከዚህ የሚከተሉት አንዱ የደም መርጋት አነስተኛ ችግር ለነበረባቸው ሰዎች፤ የሰረብራል ቨኑስ ሳይነስ ትሮሞሲስ፤ የሀፓሪን ማነቃቂያ ትሮምቦችይቶፐና፤ idiopathic splanchnic thrombosis ወይም antiphospholipid syndrome with thrombosis ላለባቸው ሰዎች የComirnaty (Pfizer) ክትባት ይመረጣል።

ባለፈው ጊዜ ሌላ ዓይነቶች የደም መርጋት ከነበረብዎት፤ እንደ ጥልቀት ያለው የቨን deep vein thrombosis (DVT) ወይም pulmonary embolism (PE) ወይም ለደም መርጋት ችግር ምክንያት ቢኖርብዎትም አሁንም የ AstraZeneca ክትባት መውሰድ ይችላሉ። ባለፈው ጊዜ ሌላ ዓይነቶች የደም መርጋት የነበረባቸው ሰዎች ለ TTS ችግር የሚፈጥር ወይም ይህ ከተፈጠረ በበለጠ ህመም መፈጠር የሚያሳይ መረጃ የለም። በአጠቃላይ ለ AstraZeneca ክትባት በጥልቀት ለተጠቀሙ አገሮች ስለ የደም መርጋት መጠን አልተጠቀሰም።

የሚከተለው ሁኔታዎች ላለባቸው ሰዎች የAstraZeneca COVID-19 ክትባትን ማግኘት ይችላሉ:

- በሆነ ሰውነት አካል ላይ የደም መርጋት ላለባቸው
- የመርጋት ሁኔታ መከሰት ለጨመረና ለመቋቋም የበሽታ መቋቋም ሀይል ለሌለው
- የደም መርጋት ችግር ያለበት ቤተሰብ
- የአስቻሚክ/ischaemic ልብ በሽታ ወይም ደም ማቆም/ስትሮክ ላለበት
- አሁን ወይም ከዚህ ቀደም ትሮምቦስይቶፐኒአ/thrombocytopenia (አነስተኛ ፐላተለት መጠን ያለው)
- የደም ማቅጠኛ/anticoagulation ህክምና ለሚያገኙ

በብዛት የአስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባትን ለተጠቀሙ አገሮች የደም መርጋት ከመጠን በላይ እንዳልሆነ ነው። የደም መርጋት በህዝብ ላይ መፈጠር የተለመደ እንደሆነና የአስትራዘነካ/AstraZeneca COVID-19 ክትባትን ከወሰዱ በኋላ ሁሉም የደም መርጋት ይፈጠራል ማለት አይደለም። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ የደም መርጋት ከተፈጠረ፤ ሀኪምዎ ምክንያቱን ለማወቅ የደም ምርመራ ማድረግ ይችላል።

### የመጀመሪያ መጠን/dose የAstraZeneca ክትባትን ወስጀ ከነበረ ምን ይደረጋ?

በማንኛውም እድሜ ገደብ ያሉ ሰዎች የመጀመሪያውን AstraZeneca COVID-19 ክትባት መጠን/ dose ክትባት ከወሰዱ በኋላ ከባድ ችግር ካልተፈጠረ ሁለተኛውን መጠን/ dose ተመሳሳይ ክትባት መውሰድ አለባቸው። በዩናይትድ ኪንግደም/UK ጥሬ መረጃ እንደሚለው ሪፖርት እንደተደረገ በTTS ላይ የሚፈጠረው ችግር በጣም አነስተኛ እንደሆነ፤ ዛሬ ሪፖርት እንደተደረገው ከተሰጠው 22.8 ሚሊዮን ሁለተኛውን መጠን/doses የ AstraZeneca COVID-19 ክትባት ውስጥ 44 ጉዳዮች ሪፖርት እንደተደረገ ነው። ይህ ሲተረጎም በየሚሊዮን የሁለተኛ መጠን ክትባቶች የተገመተው መጠን 1.9 ጉዳዮች ይሆናል። (በዩናይትድ ኪንግደም/UK፤ በአንደኛው መጠን/doses ክትባቶች በየሚሊዮን 14.8 ጉዳዮች ሪፖርት ከተደረገው ችግር ጋር ሲነጻጸር)።

## ይህን ክትባት መውሰድ የሌለበት ማን እንደሆነ

ከዚህ በታች ያሉት ካለብዎት ይህን ክትባት መውሰድ የለብዎትም:

- ቀደም ሲል የክትባት መጠን/dose ሲወስዱ የማይስማማ/anaphylaxis (ከፍተኛ የሆነ ዓይነት አለርጂ ከተፈጠረ)
- ለማንኛውም ክትባት ይዘት ላለው ሲጋለጡ አለመስማማት/anaphylaxis፤ ይህም ፖልይሶርባትን/polysorbate 80 ያካተተ
- የካፒላርይ ማንጠብጠብ ችግር ታሪክ
- TTS የሚፈጠረው ቀደም ሲል ከተወሰደ መጠን/dose ክትባት በኋላ ይሆናል
- ቀደም ሲክል ከነበረ ክትባት መጠን ጋር አስተዋጽኦ ያለው ሌላ ከባድ ችግር ፈጠራ ካለ ነው

## ክትባቱን ከመውሰድ በፊት ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች

### ቅድመ ጥንቃቄዎች

አንዳንድ ሁኔታዎች ላሉባቸው ሰዎች ተጨማሪ ቅድመ ጥንቃቄችን ማድረግ ይኖርባቸው ይሆና፤ ይህም እንደ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ወይም በአለርጂ ልዩ ባለሙያ ምክርን ካገኙ በኋላ ክትትል ለማድረግ ለ 30 ደቂቃዎች የሚሆን መቆየት ሊኖርባቸው ይችላል። በሚከተሉት ላይ ከነበረብዎት ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎ መናገር:

- ለኮቪድ/COVID-19 ክትባት መጠን/ **dose** ወይም በክትባት ንጥረ ነገሮች ላይ **ቀደም ሲል የአላርጂ ችግር ተፈጥሮ ከነበረ**
- **ለሌላ ክትባቶች ወይም ሌላ መድሃኒቶች አለመስማማት/anaphylaxis** የሚወስዱ ከኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ጋር ያልተለመዱ ንጥረ ነገሮች ስለመኖራቸው ለማረጋገጥ የርስዎ ክትባት አቅራቢ ማጣራት ይችላል
- በአሁኑ ጊዜ ህክምና የሚያስፈልገው፤ ከማስቶስይቶሲስ/mastocytosis ጋር ለታወቀ አለመስማማት/anaphylaxis

**የመድማት ችግር ካለብዎት** ወይም እርስዎ **የደም ማቅጠኛ** (እንዳይረጋ ለሚያደርግ) **የሚወስዱ** ከሆነ፤ ለርስዎ በሽታ መከላከያ ክትባት/ immunisation አቅራቢ መናገር። እርስዎ ክትባቱን በመርፌ ተደርጎ በጅማት ስር መውሰዱ ደህንነቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ ለመወሰን የርስዎ ክትባት አቅራቢ እንደሚረዳና መርፌውን ለመውሰድ ጥሩ ጊዜ መቸ እንደሆነ ለመወሰን ይረዳል።

### የበሽታ መቋቋም አሰራር ድክመት ላለባቸው ሰዎች (የበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር/immunocompromise)

ከበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር ጋር ባሉ ሰዎች የሚያካተተው የጤና ችግር ሁኔታ ላለባቸው ወይም ላላባቸው በሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር የሚያዳክም መድሃኒቶችን ለሚወስዱ ይሆናል። ከበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር ጋር ባሉ ሰዎች ላይ የሚካተቱት ከሄችአይቪ/ HIV ጋር ለሚኖሩ ሰዎች፤ ከኮቪድ/COVID-19 በሚፈጠር ከባድ ህመም ወይም ሞት ላይ በሚያደርስ ከፍተኛ ችግር ላይ ላሉት ይሆናል።

ከበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር ጋር ላሉት ሰዎች የ AstraZeneca ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት እንዲወስዱ የአውስትራሊያ መንግሥት በጥብቅ ያሳስባል፤ ይህም እንደ 'ህይወት ያለው ክትባት' ባህሪ አያሳይም። የአደኖቫይረስ/adenovirus ተሸካሚ ተቀይሯል ስለዚህ እንደማይባዛ ወይም ወደ ሌላ ህዋስ እንደማይሰራጭና በሽታ መፍጠር አይችልም። ይህ ከበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር ጋር ላሉት ሰዎች ደህንነቱ የተጠበቀ ነው።

ለ AstraZeneca ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት የተካሄደ ሙከራዎች ከበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር ጋር ያሉትን ሰዎች አላካተተም፤ ነገር ግን የዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለባቸው በዓለም ዙሪያ ያሉት ብዙ ሰዎች ክትባቱን ወስደዋል። የተረጋጋ ኤችአይቪ/ HIV በሽታ ባለባቸው የ AstraZeneca ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት በተሰጣቸው ሰዎች ላይ የቀረበው ክሊኒካል መከራ ውጤቶች በቅርቡ እንደሚታወቅ ነው። የ AstraZeneca ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲነጻጸር በበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር ላሉት ሰዎች ምን ያህል በጥሩ እንደሚሰራ አናውቅም። ያነሰ ውጤት ሊኖረው እንደሚችልና ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ለሌላው መከላከያ እርምጃ ማለት በቀጣይነት የአካል እርቀትን መጠበቁ አስፈላጊ ነው።

በበሽታ መቋቋም አቅም ሀይል አሰራር ክትባት ስለመጠቀም ለበለጠ መረጃ በድረገጽ: [COVID-19 vaccination decision guide for people with immunocompromised] ላይ ማየት።

## ነብሰጡር ለሆኑ እና የእናት ጡት ለሚያጠቡ ሴቶች

እድሚያቸው ከ60 ዓመት በታች ለሆኑ ጎልማሶች እና ነብሰጡር ሴቶች ወይም የእናት ጡት ለሚያጠቡ ሴቶች ለ Comirnaty (Pfizer) ክትባት መውሰዱ ይመረጣል። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ የናት ጡት ማጥባትዎን ማቋረጥ የለብዎም የመጀመሪያ AstraZeneca COVID-19 ክትባት መጠን/dose ክትባትን ለወሰዱ ነብሰጡር ሴቶች ለሁለተኛ መጠን/dose ክትባት ለComirnaty ወይም ለAstraZeneca COVID-19 ክትባት መውሰድ ቢችሉም ነገር ግን ለComirnaty ክትባት እንዲወስዱ ይመረጣል።

ለነብሰጡርና ጡት ለሚያጠቡ ሴቶች ስለ ክትባት መጠቀም ለበለጠ መረጃ በድረገጽ: [COVID-19 vaccination decision guide for women who are pregnant, breastfeeding or planning pregnancy] ላይ ገብቶ ማየት።

## በኮቪድ/COVID-19 ታሪክ ላለባቸው ሰዎች

ባለፈው ጊዜ የኮቪድ/COVID-19 ከነበረብዎት፤ ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎ መናገር። ለኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ከመውሰድዎ በፊት ወደ መደበኛ ህይወትዎ ከተመለሱ እስከ ስድስት ወራት መጠበቅ እንዳለብዎት በርስዎ አቅራቢ በኩል ምክር ሊቀርብልዎት ይሆናል። በኮቪድ/COVID-19 ቀጣይ ህመም ካለብዎት፤ ክትባቱን ለመውሰድ ጥሩ ጊዜ ለማቀናጀት ከርስዎ ህክምና ሰጪ ሀኪም ጋር መነጋገር ነው።

ባለፈው ጊዜ ከኮቪድ/ COVID-19 ታሪክ ጋር ለሆኑ ሰዎች ከሁለቱ ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ምልክት ዓይነት አንደኛውን መጠቀም ይቻላል።

## AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት እና ህጻናት

እድሚያቸው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ለሆኑ የ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ጊዜያዊ ፈቃድ ብቻ እንዳገኘ እና ለታዳጊ ወጣቶች መስጠት እንደማይቻል ነው። የኮቪድ/COVID-19 ችግር በተለይ ከባድ በሽታ የሚከሰተው ከታጋዲ ጎልማሶችና በእድሜ አንጋፍፋ ከሆኑ ጎልማሶች ጋር ሲነጻጸር በህጻናት ላይ ያነሰ ነው።

## የክትባት ደህንነትና በተቃራኒ ለሚከሰቱ ድርጊቶች ሪፖርት ስለማድረግ

በአውስትራሊያ ውስጥ ላሉት ክትባቶች በሙሉ የህክምና ጥራይ አስተዳደር (TGA) ግምገማ ማጣሪያ ያካሂዳል። አንድ ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀ፤ በጥሩ እንደሚሰራና በጣም በከፍተኛ ጥራት ደረጃ የተመረተ ስለመሆኑ (TGA) በማረጋገጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያደርጋል። ለኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ተቀባይነት ማስገኛ አሰራር ሂደት መግለጫ የሚቀርበው በድረገጽ [TGA website] ላይ ነው።

የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ደህንነት በቀጣይነት ቁጥጥር የሚደረገው በኮቪድ/COVID-19 ክትባት መስጫ ፕሮግራም በሚካሄድበት ጊዜ ይሆናል። ሊከሰት በሚችል ችግር ላይ ጥርጣሬ ለርስዎ ክትባት አቅራቢ ወይም ለሌላ ጤና ጥበቃ ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ ይቻላል። ከዚያ እርስዎን ወክለው ለርስዎ አስተዳደር ግባት ወይም ተሪቶርይ ጤና ጥበቃ መምሪያ ወይም በቀጥታ ለህክምና ጥራይ አስተዳደር (TGA) መደበኛ ሪፖርት ያቀርባሉ።

በራስዎ ይህንን ሪፖርት ለማቅረብ የሚፈልጉ ከሆነ፤ እባክዎ ከኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች ጋር ሊከሰት ስለሚችል ችግር ጥርጣሬ እንዴት ሪፖርት እንደሚደረግ መረጃ በድረገጽ [TGA website] ላይ ገብቶ ማየት።